ነው። ደጋግመን እንደገለጽነው ዋናውን ውሣኔ መሠረት ተደርጎ የተከናወነ አፈፃፀም የለም። እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ ውሣኔ እንዲፈጸም የሚቀርበው ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል እስካልተባለ ድረስ እንዴ ትዕዘዝ ተሰጥቶአልና ከዋናው ውሣኔ ውጪም ቢሆን አይነካም ብሎ ማለፍ የሚቻል /የሚገባም/ አይደለም። ይህ ዓይነቱ አካሄድ ሁለት መሠረታዊ ግድፈቶች አሉት። የመጀመሪያው እንደ ውሣኔው እንዲፈጸም የቀረበውን ጥያቄ የሕግ ምክንያት ሳይኖር ተቀባይነት እንዳ ኖረው ማድረግ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በውርስ ሃብቱ ላይ እኩል መብት ያላቸውን ወገኖች /አመልካቾችና ሌሎች ወራሾች/ ከሕግ አግባብ ውጪ ተካፋይ እንዳይሆኑ ማድረግ ነው። ስናጠቃልለው አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ የአፈፃፀም ክርክር የተነሳበትን ዋናውን ውሣኔ መሠረት ያላደረገ እና ውሣኔው የሚፈጸምበትን ሁኔታ ያላሣየ በመሆኑ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

## ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 622/98 ጥር 14 ቀን 99 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል።
2. አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ዋናውን ውሣኔ /የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው/ መሠረት በማድረግ የውርሱን ሃብት አውራሾች እንዲያከፋፍል ወስነናል። ይፃፍ።
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ። መዝገቡ ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 29653

መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሠ ይርጋ

**አመልካች፡-** 1. አቶ ነጋ ደምስ
2. አቶ ኃይሉ ደምስ } ቀረቡ።

ተጠሪ፡- 50 አለቃ አዲሱ ደምስ - ቀረቡ።

## ፍ ር ድ

ለሠበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ነው። የአሁኖቹ አመልካቾች ከሥር አፈፃፀም ባለዕዳ ጋር ተከራክረው ካስወሰኑ በኋላ በውሣኔው መሠረት እንዲፈፀምላቸው የአፈፃፀም ክስ አቅርበዋል። ፍ/ቤቱም በውሣኔው መሠረት ለማስፈፀም የውርስ ንብረት የሆነውን ቤት በሀራጅ አሸጦ ከሽያጩ የተገኘውን ገንዘብ ለማከፋፈል በሒደት ላይ እንዳለ የአሁኑ ተጠሪ እሣቸውም የቀኝ አዝማች ደምስ አስፋው የልጅ ልጅ መሆናቸውንና እናታቸውን ወ/ሮ ይርገዱ ደምስን ተክተው ሊወርሱ እንደሚገባ ገልፀው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ጣልቃ ገብተው ለመከራከር ጠይቀዋል። ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካቾች የአፈፃፀም ባለዕዳ የሆኑትን ወ/ሮ እስከዳር ደምስን ከሰው ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ በውርሱ ቤት እስከ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ሲከራከሩ ጣልቃ ገብተው ያልተከራከሩና በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ለመቃወም መብት የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ ጥያቄያቸውን ውድቅ አድርጓል።

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ የአያታቸው ፊትአውራሪ ደምስ አስፋው የልጅ ልጅ በመሆናቸው እናታቸውን ተክተው ሊወርሱ ስለሚገባ ከተሸጠው ከፊታውራሪ ደምስ አስፋው ቤት ድርሻ ገንዘቡን ሊያገኙ ይገባል በማለት የመጀመሪያውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

ይህ ችሎትም የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት ቀርቦ የሚጣራ ነጥብ ያለው መሆኑን ስላመነ መ/ሰጪዎቹን አስቀርቧል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

እኛም መዝገቡን መርምረን እንደተረዳነው ክርክሩ የአፈፃፀም ክርክር ነው፡፡ አመልካቾች የሥር የአፈፃፀም ባለዕዳዋን የአባታቸውን የፊታውራሪ ደምስ አስፋውን ቤት አስመልክተው ከሠው አስፈርደዋል፡፡

ይህ የውርስ ቤት የአመልካቾች እናት እና አባት በመሆኑ አመልካቾቹ የሁለቱንም ወላጆችቻቸው ድርሻ የፍ/ባለዕዳዋ ደግሞ የአባታቸውን ድርሻ ብቻ እንዲያገኙ በተሰጠው ውሣኔ መሠረት ለማከፋፈል ጉዳዩ በአፈፃፀም ደረጃ ደርሶ ቤቱ በሀራጅ ተሸጦ ገንዘቡ ተይዟል፡፡ እንግዲህ በዚህ ደረጃ ነው ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት መቃወሚያ ያቀረቡት፡፡ በመሠረቱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለው አንድን ውሣኔ ለማስፈፀም ንብረት ሲያዝ በንብረቱ ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ሰው ይህ ንብረት እንዳይያዝ ወይም እንዳይከበር ነው፡፡ ይህ የስነ ስርዓቱ ድንጋጌም የሚመለከተው ለፍርዱ ምክንያት የሆነን ንብረት ሣይሆን ገንዘብ እንዲከፈል የተሰጠን ውሣኔ ለማስፈፀም የተያዘን ንብረት ነው፡፡ ንብረቱ ፍርድ ያረፈበት ከሆነ ግን መብቴ ተነክቷል የሚለው ወገን አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት ውሣኔው ከመፈፀሙ በፊት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት ፍርዱን ለፈረደው ፍ/ቤት ነው በመሆኑም



በዋናው ክርክር ገብቶ ተከራክሮ ውሣኔ ያላገኘ ተከራካሪ ወገን በአፈፃፀም ጊዜ ውሣኔ እንዲፈፀምለት ጥያቄ የሚያቀርብበት የሕግ መሠረት የለም፡፡

በተያዘው ጉዳይም ቢሆን አመልካቾች የፍ/ባለዕዳዋን ከሰው አስወስነው ውሣኔውን በማስፈፀም ላይ ይገኛሉ ተጠሪ ውሣኔው መብታቸውን የሚነካ ከሆነ ውሣኔውን በመቃወም ቀርበው እንዲሻሻል ወይም እንዲለወጥ ማድረግ ነበረባቸው በመሆኑም በውሣኔው ያላገኙትን መብት በአፈፃፀም እንዲከበርላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት ቀዳሚነት መብት የሌላቸው መሆኑን እያረጋገጠ የውርስ ንብረት እንዲካፈሉ ሲል የሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት የለውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10050 መጋቢት 11 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04241 በሐምሌ 13 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ